**ሕገ መንግሥቱን በመጣስና የሕግ የበላይነትን በመርገጥ ዛሬም የዜጎችንና የቡድን መብቶችን በመደፍጠጥ ላይ ያለው የኢህአዴግ መንግሥት ከፀረ ህዝብ ተግባሩ መቆጠብ ይኖርበታል፡፡**

(ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ የተሰጠ መግለጫ)

መድረክ የሀገራችንን ወቅታዊ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ሁኔታዎችን አስመልክቶ መግለጫዎችን ሲሰጥ መቆየቱ ይታወቃል። በቅርብ ሳምንታትም በ12ኛ መደበኛ ጉባኤው እና ከዚያም ወዲህ በተለያዩ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ መግለጫዎችን በማውጣት በሀገራችን ያለውን የሕግ የበላይነት መታጣት፣ የሕገ መንግሥት አለመከበርን በሚመለከት ሊታረሙ የሚገቡ ጉዳዮችን አስረግጦ አመላክቷል።

በእነዚህ መግለጫዎቻችንም ኢህአዴግ በአዲስ አበባ ከተማ በሳሪስ፣ በቦሌ ቡልቡላና ወረገኑ በተባሉ አካባቢዎች ከ2000 በላይ የመኖሪያ ቤቶች በማፍረስ ቤተሰቦቻቸው መበተናቸውንና በዜጎች ሕይወትም ጉዳት መድረሱን መኮነናችንን ማስታወስ እንወዳለን፡፡ እንደዚሁም የዜጎቻችንን ቤቶች በማፍረስ በብዙ ሺህዎች የሚቆጠሩትን ዜጎች አፈናቅሎ ቤት አልባ በማድረግና የሰዎችን ሕይወት በመቅጠፍ የተደረገውን ኢ-ሰብአዊና ወንጀለኛ ድርጊት በመኮነን፣ ወንጀል የፈጸሙ ወገኖች በሕግ እንዲጠየቁና ጉዳት ለደረሰባቸውም ወገኖች መንግሥት ካሣ እንዲከፍል ጠይቀናል፡፡ ነገር ግን እንዲህ ዓይነቱን ኃላፊነት የተላበሰ የእርምት እርምጃ ጥቆማዎችንና የመብት ጥያቄዎችን ኢህአዴግ ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ፣ ይልቁንም ወከባን፣ ማሳደድን፣ እሥራትንና ግድያውን አጠናክሮ ቀጥሎበታል። ለዚህ ኃላፊነት ለጎደለው እርምጃዎቹ ማሳያ የሚሆኑ ብዙ ክስተቶች አሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ኢህአዴግ በማንአለብኝነት ባለፉት ሳምንታት በሃና ማርያም አካባቢ ዜጎች ለረዥም ዓመታት የኖሩባቸውን ቤቶች ሁሉ «ሕገ ወጥ» በማለት የማፍረስ ዘመቻው የብዙ ሺህ ዜጎች የመኖሪያ ቤቶችን ጭካኔ በተሞላበትና አስተውሎት በጎደለው ሁኔታ በዶዘርና በግሬደር ታግዞ ማፍረሱ ነው፡፡ በዚህም እርምጃው በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎቻችንን ያለ ጎጆ በማስቀረት፣ ለክረምት ዶፍና ጎርፍ አጋልጦአቸዋል። በዚሁ ዘመቻውም የዜጎች ሕይወት መጥፋቱ የሚታወቅ ሲሆን፣ መንገድ በመዝጋትም ወላጅን ከህፃናት በመለየት ጭምር በብዙ ሺህዎች የሚቆጠሩ ዜጎች እንዲጉላሉ አድርጓል። እንዲህ ዓይነቱ ሕዝብን ከመጤፍ ያለመቁጠርና ትዕቢት የተሞላበት ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቱ ዛሬ ከመቼውም በላይ የኢህአዴግ የዕለት ተዕለት ተግባር ሆኖአል።

ከዚህ በፊት ያነሳነውን መሠረታዊ ጉዳይ ደግመን ለማንሳት፣ እነዚህ "በሕገ ወጥነት" ቤት ገንብተዋል የተባሉት ዜጎች፣ ቤት መሥራት [illegible] የማግኘት መብታቸውን ለመጠቀም

መድረክ
FORUM
The Ethiopian Democratic Unity

በሚመለከታቸው መንግሥተዊ መ/ቤቶች ለረጅም ዓመታት ሲንከራተቱ ቆይተው ተስፋ ቆርጠው በቀድሞ የመሬት ባለይዞታዎች የተሠሩትን ደሳሳ ጎጆዎች በመግዛት፣ ለኑሯቸው በሚመች መልኩ ሠርተው፣ መብራትና ውሃ እስከ ማስገባት የደረሱ ሁሉ ያሉበትና ግብር እየገበሩ ከአምስት ዓመታት በላይ በቦታው ላይ የኖሩ ሁሉ እንዳሉበት ታውቋል። መሬት የሕዝብና የመንግሥት ነው ከተባለበት ከደርግ ዘመን ጀምሮ፣ ሁሉም የከተማ ነዋሪ የመኖሪያ ቤት መሥሪያ ቦታ /መሬት/ በነፃ ባገኘበት ሀገር፣ እነዚህ ዜጎች ከአምስት ዓመታት በፊት በሠሩዋቸው ቤቶች መኖራቸው እንደ ከባድ ወንጀል ተቆጥሮ፣ ግምት ሳይከፈላቸውና አማራጭ ሳይዘጋጅላቸው በከፍተኛ ጭካኔ ሥርዓት አልባ በሆነ ሁኔታ ቤቶቻቸውን ማፍረስ፣ ፀረ ሕዝብነት በመሆኑ መድረክ እርምጃውን ዳግመኛ አጥብቆ ይኮንናል።

ከዚህ በተጨማሪ፣ በዜጎች ላይ እየተፈጸሙ ያሉት የፖለቲካ እንደምታ ያላቸው ሕገ-ወጥ ግዲያዎች መድረክን ዘወትር እያሳሰበው ነው። በዚህ ረገድ በዚሁ ቅርብ ቀናት የኢህአደግ ታጣቂዎች በዳንዲ ወረዳ በጊንጪ ከተማ ተማሪ እሸቱ ወርቁ ሞረዳን ከመግደላቸውም ሌላ ሌሎች ወጣቶችን በማቁሰል፣ በአምቦ፣ በጉደር፣ በተኬ፣ በጌዶና አካባቢዋ የወከባ፣ የእሥራትና የማሣደድ ዘመቻውን ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ሁኔታ አጠናክረው ቀጥለዋል። ሰሞኑንም በቡኖ ዞን በደሌ ከተማ ዘይኑ ቤኩማ የተባለው አባላችንና ባለፈው ምርጫ ታዛቢ የነበረው በጦር ተወግቶ ጉዳት ደርሶበታል።

በደቡብ ክልልም በጋሞጎፋ ዞን በአርባምንጭ ዙሪያ ወረዳ 28፣ በዛላ ወረዳ 14፣ ኡባ ደብረ ፀሐይ 10 አባሎቻችን የሆኑ አርሶ አደሮች ያለአግባብ ታሥረው በዚህ የአዝመራ ወቅት ግፍ እየተፈፀመባቸው ይገኛል። በሐዲያ ዞንም በተደጋጋሚ አባሎቻችንን በማሠር ተመሳሳይ ሁኔታዎች ተፈጽመዋል።

ከላይ በተጠቀሱት አካባቢዎችና በሌሎችም በአብዛኛው የሀገራችን ክልሎች ወቅቱ የዘር ወቅት መሆኑ እየታወቀ ለደጋፊዎቻችንና አባሎቻችን ማዳበሪያ በመከልከልና "መድረክ ይስጣችሁ" በማለት የኢህአዴግ ካድሬዎች የዘር ወቅት እንዲስተጓጎል እያደረጉ ነው። ከዚህም ሌላ መሬታችን ማዳበሪያ አይፈልግም የሚሉትን ገበሬዎች በበንች ማጂ፣ በከፋ፣ በዳውሮ፣ ወዘተ ዞኖች ኢህአደግ የንግድ ግብዓት የሆነውን ማዳበሪያ በግድ ውሰዱ እያሉ ቁም ሥቅላቸውን እያሳየ ይገኛል። ይህ በደመ ነፍስ ተግባር ላይ እየዋለ ያለው የማዳበሪያ ስርጭት ወከባ የሞላበት እንደመሆኑ በአስቸኳይ መቆምና ሥርዓት መያዝ አለበት።

እንደዚሁም በሰላም፣ በሠለጠነና ሕዝቡን አሳታፊ በሆነ መንገድ ችግሮችን የመፍታቱ ብቃትም ሆነ ፍላጎቱ የሌለው ኢህአዴግ ሰሞኑን "በሠርጎ-ገብ የኤርትራ መንግሥት ተላላኪዎች" ላይ በጎንደር ከተማ ወሰድኩ ባለው ወታደራዊ እርምጃ፣ በራሱ የመገናኛ

ብዙሃን እንደገለጸው፣ለማመን በሚያዳግት ደረጃ ቁጥራቸው የበዛ ዜጎች ሕይወታቸውን አጥተዋል፡፡ የእነዚህን ዜጎች ሕይወት በከንቱ መቀጠፍን ያስከተለው በመድረክ እምነት ሁኔታዎች ከርረው ለግጭት ከመብቃታቸው በፊት ከህዝቡ ለሚነሡ ጥያቄዎች በሕገ-መንግሥቱ አግባብ ፈጥኖ መልስ አለመስጠትና በጉዳዩ ህዝቡን አለማሳመን ነው፡፡ ከዚህ አልፎ የሄደም ጉዳይ ቢሆን እንኳን በሕግ-የበላይነት አግባብ በሰላም ለመፍታት መሞከር ነው፡፡ ነገር ግን ኢህአዴግ "ሠርጎ-ገቦች" ያላቸው ወገኖች በታላቂዋ ጥንታዊት ከተማ ጎንደር እንደዚህ በጦር መሣሪያ ተደራጅተው ፊልሚያ እስኪጀምሩ ድረስና ነዋሪነታቸው ጐንደር ከተማና ደባርቅ የሆነ አንዳንድ የትግራይ ተወላጆች ተለይተው ንብረቶቻቸው የብአዴን ሰንደቅ ዓላማ ቢያዙ ቡድኖች ሲወድሙ ፖሊስ፣ድህንነቱና ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ የት ነበሩ? እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ ጥያቄዎች በመመለስ ኢህአዴግ የሰጠውን ቁንጽል መግለጫ ትቶ ስለ ጉዳዩ ዝርዝር ማብራሪያ ለሕዝባችን በስፋትና በጥልቀት መስጠት እንዳለበት አበክረን እናስገነዝባለን፡፡

ሌላው መድረክን በእጅጉ የሚያሳስበው፣መላው የአገራችን ዜጎች ዛሬ ምሬታቸው ጫፍ ደርሶ ለሚደርስባቸው በደል ምላሽ የሚሰጥ አካል በጠፋበት ሁኔታ ውስጥ መገኘታችን ነው፡፡ ሁኔታውም እየከፋ ሄዶ በየክልሉ፣በየገጠሩና በየከተማው የሚሰማው የሕግ የበላይነት ያለህ የሚል የሠቆቃና የዋይታ ድምጽ እጅግ የሚያሳስብ ሆኖአል፡፡

ስለሆነም ኢህአዴግ በዚህ መግለጫ ለተነሡ ጉዳዮችና ቀደም ሲልም በመግለጫዎቻችን ለተጠቀሰት ሀገራዊ ጉዳዮች በአስቸኳይ ምላሽ እንዲሰጥ አጥብቀን እያሳሰብን፣መላው ሕዝባችንም እንደትናንቱ ሁሉ ዛሬም ለምናካሂደው ሰላማዊና ሕገ-መንግሥታዊ ትግላችን ሁለንተናዊ ድጋፍ በመስጠት በህዝባዊ እንቅስቀሴያችን ውስጥ በመሰለፍ ከጎናችን እንዲቆም ዛሬም ሀገራዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

ድል ለሰላማዊ ዲሞክራሲያዊ ትግላችን!

ሐምሌ 15 ቀን 2008 ዓ/ም

አዲስ አበባ